# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

**የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት በመስጠት ለተሰማሩ አካላት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 167/2017 አስፈላጊነቱ ማብራሪያ**

**መግቢያ፡-**

አዲስ አበባ ከተማ ብዙ ሚሊየን ህዝብ የሚኖርባት፣ የአፍሪካ መዲና፣ የበርካታ አለማቀፍ ተቋማት፣ዲፕሎማቶች እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አካታ የያዘች ከተማ በመሆኗ ከፍተኛ መጠን ያለው ደረቅ ቆሻሻ ይመነጭባታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፅዳት አገልግሎት ኤጀንሲም በከተማው ያለውን የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ የማስተዳደር ስልጣን ያለውና በአዋጅ የተቋቋመ ተቋም ነው (በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 84/2016) ፡፡ ኤጀንሲው ከመቼውም ጊዜ በተሻለ መልኩ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አጓጓዝና አወጋገድን በማዘመን የከተማዋ ጽዳት በሚፈለገው ደረጃ እንድትደርስ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ለማጓጓዝ በመንግስት አቅም ብቻ ሊሰራ የማይችል መሆኑን ከግምት በማስገባት የግሉ ዘርፍ እና ማህበራት በማደራጀት እንዲሰማራ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሰረት በርካታ ደረቅ ቆሻሻ አገልግት ሰጪ አካላት ፈቃድ አውጥተው እንዲሰሩ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ አገልግሎት ሰጪ አካላት የሚሰጡትን የአገልግሎት ጥራት ለመጨመር እና የሚፈጠሩ የአሰራር ግድፈቶችን በዘላቂነት ለማረም የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥበትን ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ መመሪያ እንዲዘጋጅ አሰፈልጓል፡፡

*የመመሪያ አላማ፡-*

## *የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት በመስጠት ለተሰማሩ አካላት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ አፈጻጸም መመሪያ*

1. *በከተማው የሚመነጨ ደረቅ ቆሻሻ ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት እንዲውል ወደ ሀብትነት በመቀይር የሚወገደውን ደረቅ ቆሻሸ መጠን በመቀነስ ለኃይል ማመንጨነት እንዲውል ደረቅ ቆሻሻ በተገቢው እንዲሰበሰብ ማድረግ*
2. *አጀንሲዉ ደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪ አካላት ስራቸውን በአግባቡ እያከናወኑ መሆኑን ለመከታት እንዲችል ማድረግ፤*
3. *ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ፣ በማጓጓዝ ወይም መልሶ በመጠቀምና ኡደት በማድረግ ላይ ለመሰማራት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አካላት/ባለሀብቶች በመስፈርት መዝኖ የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት፣ የስራ ፈቃድ፣ የብቃት ማረጋገጫ እድሳት እና የስራ ፈቃድ እድሳት ለመሰጠት፤*
4. *ኤጀንሲዉ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎቱን በአግባቡ መፈጸሙን በመከታተል አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ፣ ከመመሪያ ውጪ በሚፈጽሙት ላይ የእርምት እርምጃዎች እንዲውስድ፣ ተፈፃሚነቱን እንዲከታተል ማስቻል፤*
5. *የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎቱን በጥራት በማይሰጡ አካላት ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ኤንስዉ የሚወስድበትን አግባብ ማስቀመጥ*

## ***<u>ማጠቃለያ</u>***

*የደረቅ ቆሻሻ መለየት እና ማጓጓዝ አሰራር መመሪያ፤ የመልሶ መጠቀም ማህበራት ሸርክና የሚሰበስቡበት ተቋም  እና አሰራር መመሪያ  የለም ፤የመልሶ መጠቀም ማህበራት ሰርተፊኬት አሰጣጥ እና ውለታ እና የሚፈጽሙበት መመሪያ ደረቅ ቆሻሻ ማቆያ አያያዝና ማጓጓዝ አስተዳደር መመሪያዎች መውጣት ሲኖርባቸው ባለመውጣታቸው የተቀመጡ እቅዶችን ለማሳካት ግልጽ  የሆነ አቅጣጫ ከመስጠት ይልቅ ስራን በዘፈቀደ ለመምራት ዳርጓል፡፡*

ስለሆነም መመሪዎቹ ቢዘጋጁ እና ስራውን መምራት ቢቻል እንዲሁም የከተማውን መዘመን ተከትሎ መከለስ ያለባቸው መመሪያዎች በአዋጅ 84/2016 መሰረት መከለስ እንደላባቸው ታይቷል፡፡ በሌላ በኩል ባለድርሻ አካላትን በተመለከተ በአብዛኞቹ የተሰጣቸውን ሀላፊነት ተግበራዊ አለማድረግ ውስንነቶች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡